# የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ሚና በሰነደ ሙአለ-ንዋዮች ግብይት ስነምህዳር

***መግቢያ***

***ግብይት እና የሰው ልጅ ተነጣጥለው የማያውቁ ናቸው ቢባል እውነትነቱን የሚጠራጠር ይኖራል ተብሎ አይገመትም። እናም ግብይት ከሰው ልጅ ጥንታዊ ተግባራት አንዱ ነው ለማለት ይቻላል። ግብይት በተለመዱና ቀላል በሆኑ ሸቀጦች ተጀምሮ ውስብስብ እስከሆኑ እቃዎች እና አገልግሎቶች ከመሻገሩም በላይ በአሁኑ ጊዜ የገንዘብ ዋጋ ያላቸውን ልዩ ልዩ ሰነዶች የምንገበያይበት ደረጃ ላይ ደርሷል።***

***የገንዘብ ዋጋ ያላቸው ሰነዶች ግብይት መስፋፋት የተማከለ የሰነደ ሙአለ ንዋዮች ግብይት ስርአት እና ግብይቱን የሚመሩ ህግጋት እንዲበጁ ምክንያት ሆነ። ከእንደዚህ አይነት ገበያዎች አንዱ የካፒታል ገበያ ነው። በቀላል አገላለፅ የካፒታል ገበያ ከአለታዊ ፍጆታ የተረፈ ገንዘብ ያላቸው (አቅራቢዎች) እና ለልዩ ልዩ ኢንቨስትመንት ገንዘብ የሚፈልጉ ሰዎች ወይም ኩባንያዎች የሚገናኙበት መድረክ ነው ማለት ይቻላል። አቅራቢዎች የምንላቸው የካፒታል ገበያን ተጠቅመው ብድር ለመስጠት ወይም ኢንቨስት ለማድረግ ገንዘብ የሚያቀርቡ ሰዎች ወይም ተቋማት ናቸው። በአንጻሩ ከዚህ ገበያ ካፒታል ለማግኘት የሚፈልጉት ደግሞ ኩባንያዎች፣ መንግስታት እና ግለሰቦች ሊሆኑ ይችላሉ። በመሆኑም የካፒታል ገበያ አክሲዮኖችን፣ የግምጃ ቤት ሰነዶችን እና ሌሎች የገንዘብ ዋጋ ያላቸው ሰነዶችን በቀላሉ ለመገበያየት ይጠቅማል።***

***በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ስርአት እውን መሆን ዋነኛ ምክንያቶች መካከል የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ስብራቶች ማከሚያ ከሚሆኑ ጉዳዮች እንደ አንዱ መቆጠሩ ነው። ይህ ስርአት እውን እንዲሆን፣ የሚገነባው የካፒታል ገበያም ውጤታማነት እንዲረጋገጥ፣ ገበያው አስተማማኝ ለኢንቨስትመንት የሚውል ሃብት ምንጭ እንዲሆን፣ እንደዚሁም የኢንቨስተሮች መብት እና ጥቅም ተገቢ ጥበቃ እንዲያገኝ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት መመስረት ፋይዳው የጎላ ነው።***

***የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት መደራጀት እና ጠቀሜታ***

***የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር*** 1248/2013 ***አንቀጽ*** 64 ***እና ተከታዮቹ መሰረት የተቋቋመ ገለልተኛ፣ የራሱ በጀት በመንግስት የሚመደብለት፣ የፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ ዳኛ እና ዳኞች በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙለት፣ ስላከናወናቸው የዳኝነት ተግባራት በአመት አንድ ጊዜ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሪፖርት ማቅረብ የሚጠበቅበት፣ የዳኝነት ስራውን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ሰራተኞች (ሬጅስትራርን ጨምሮ) ያሉት ራሱን የቻለ ተቋም ነው።***

የካፒታል ገበያ አዋጅ የፍርድ ቤቱን ሰብሳቢ ዳኛ እና ምክትል ሰብሳቢ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኝነት የሚያበቃ የትምህርት ዝግጅት እና የሥራ ልምድ እንዲኖራቸው የሚያስገድድ ከመሆኑም በላይ በካፒታል ገበያ፣ በንግድ ስራ፣ በሂሳብ አያያዝ እና ተያያዥ ሞያዎች እውቀት እና ልምድ ያላቸው እንዲሆኑ ይጠይቃል። በተመሳሳይ ዳኞቹም ህግን ጨምሮ ለካፒታል ገበያ ስራዎች ተዛማጅነት ባላቸው ሞያዎች በቂ እውቀት እና ልምድ ያላቸው እንዲሆኑ ያስገድዳል።

የካፒታል ገበያ ጉዳዮችን ብቻ የሚመለከት ልዩ ፍርድ ቤት ማቋቋም በበርካታ አገራት የተለመደ እና ከውጤታማነት አንጻርም ስኬቶች የተመዘገቡበት አሰራር ነው። በርከት ያሉ አገራትን ከሩቅም ከቅርብም በምሳሌነት መጥቀስ የሚቻል ቢሆንም ካናዳ፣ ህንድ እና ናይጄርያ መሰል ተሞክሮ ያላቸው አገራት መሆናቸውን መመልከት ይቻላል።  በሌላ በኩልም የአገራችን ህገ-መንግስትም ከመደበኛው ፍርድ ቤት ውጪ ሌሎች ፍርድ ቤቶች በአዋጅ እንዲቋቋሙ የሚፈቅድ ከመሆኑም በላይ ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው ልዩ ፍርድ ቤቶች የማቋቋም የቀደመ ልምምድም አለን።

የአስተዳዳር ፍርድ ቤቱ ሥራ ከጀመረበት በ2017ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ በ2027 ዓ.ም በካፒታል ገበያ ስነ-ምህዳር አፍሪካዊ የፍትህ ተምሳሌት የመሆን ርዕይ አንግቦ እየሰራ ይገኛል። አላማውም በካፒታል ገበያ ሥነ-ምህዳር ውስጥ ለሚነሱ አለመግባባቶች ለተከራካሪ ወገኖች በገለልተኝነት ታዓማኒ እና ፈጣን ውሳኔዎችን በመስጠት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ስርአቱን ጤናማነት እና ታዓማኒነት ማስጠበቅ ነው።

ፍርድ ቤቱ ለገበያው ተሳታፊዎች ብሎም በአጠቃላይ ለግብይት ስርአቱ ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች አንዱ የካፒታል ገበያ አዋጅ ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች የላቀ የአፈፃፀም ቅልጥፍና ተለማጭ (flexible) የዳኝነት ስነ-ስርአት እና ልዩ የሞያ ብቃት እንዲኖረው ማድረጉ ነው። ለምሳሌ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ ከ3 ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ እንዲሰጥ አዋጁ ያስገድደዋል። እዚህ ላይ ጊዜ እራሱ ገንዘብ መሆኑን ልብ ይሏል።

ተለማጭ (flexible) የዳኝነት ስነ-ስርአት የሚከተል፣ በዘርፉ ልዩ ሙያ ልምድና እውቀት ባላቸው ዳኞች የሚመራ እንዲሁም ተገማች እና ፈጣን ውሳኔ መስጠት የሚችል የካፒታል ገበያ ፍርድ ቤት መኖር እንደ አገር ኢንቨስተሩን ከማበረታት እና የካፒታል ገበያውን ተዓማኒነት ከማረጋገጥ በዘለለ የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለመሳብ እና ለማቆየት የሚደረገውንም ጥረት በእጅጉ እንደሚያበረታታ ይታመናል። በመሆኑም ከካፒታል ገበያ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች ቢተው በረጃጅም ቀጠሮዎች እና በሚከተሉት ጥብቅ የዳኝነት ስነ-ስርአት ምክንያት ውሳኔዎች ለአመታት ሊዘገዩ ስለሚችሉ በኢንቨስተሮች ላይ የሚደርሰው ኪሳራና ጉዳት ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ በግብይት ስርአቱ ላይ ዜጎች የሚኖራቸውን እምነት በእጅጉ ይሸረሽራል።

ከዚህ አንጻር እንደ ኬንያ፣ ታንዛኒያ፣ ዛምቢያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ናይጄሪያ፣ ካናዳ እና ሌሎች ሃገራት ተሞክሮ እና ልምድ በመቀመር የካፒታል ገበያ ጉዳዮች ተለዋጭ የዳኝነት ስነ-ስርአት የሚከተል፣ ፈጣን ውሳኔ የሚሰጥ፣ ስርአቱ

የሚፈልገው የሞያ ብቃት ያለው ልዩ ፍርድ ቤት የሚፈልጉ በመሆኑ በካፒታል ገበያ ውስጥ የሚፈጸሙ ጥፋቶችን በይግባኝ መርምሮ የመወሰን ሥልጣን ከፍ ብሎ በተጠቀሰው አዋጅ ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ተሰጥቶታል።

**የፍርድ ቤቱ የዳኝነት ስልጣን**

ፍርድ ቤቱ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ወይም የባለስልጣኑን ተግባርና ስልጣን የሚያስፈጽም ሰው የካፒታል ገበያ አዋጅን፣ አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን እና መመሪያዎችን እንዲሁም አግባብነት ያላቸው ሌሎች ህጎችን ተመስርተው የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች ተከትሎ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በይግባኝ መርምሮ የማጽናት የመሻር ወይም የመሰለውን ሌላ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ተሰጥቶታል። ውሳኔዎቹም በሚከተሉት አካላት እና ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ይሆናል።

1. በባለስልጣኑ እና በሰነደ ሙአለ-ንዋይ ገበያው ወይም ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች፣
2. በባለስልጣኑና በግብይት ተሳታፊዎች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች፣
3. በግብይት ተሳታፊዎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች
4. በግብይት ተሳታፊዎች እና በደንበኞቻቸው ኢንቨስተሮች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች፣
5. በግብይት ተሳታፊዎች እና ራሳቸውን በራሳቸው በሚቆጣጠሩ ድርጅቶች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች፣
6. በተመዘገቡ (የህዝብ) ኩባንያዎች እና በባለስልጣኑ ወይም በሰነደ ሙዓለ-ንዋይ ገበያው ወይም ራሳቸውን በራሳቸው በሚቆጣጠሩ ድርጅቶች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች፣
7. በባለስልጣኑ እና በባለስልጣኑ የሰነደ ሙዓለ-ንዋይ ምዝገባ  በተከለከለ አውጪ ወይም ኩባንያ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች፣
8. በባለስልጣኑ እና በባለስልጣኑ የተሰጠው ፈቃድ ወይም እውቅና በታገደበት ወይም በተሰረዘበት ሰው መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች፣
9. በሰነደ ሙዓለ-ንዋይ ገበያው እና ሰነዱ በገበያው ምዝገባ ተቀባይነት ያጣበት ሰው ወይም ኩባንያ መካከል፣
10. በሰነደ ሙዓለ-ንዋይ ገበያው እና ሰነደ ሙዓለ-ንዋዮቹ በገበያው እንዳይሸጡ የታገደበት ኢንቨስተር ወይም ኩባንያ፣
11. በሰነደ ሙዓለ-ንዋይ ገበያው እና ሰነደ ሙዓለ-ንዋዮቹ ከገበያው መዝገብ የተሰረዙበት ኢንቨስተር ወይም ኩባንያ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች፣
12. በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪው ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ እና በእነሱ ድርጊት የገንዘብ ጉዳት በደረሰበት ኢንቨስተር በተጠየቀ የካሳ ፈንድ ይገባኛል ጥያቄ ላይ የሚነሱ አለመግባባቶች፣ ዋነኞቹ ናቸው።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት
ECMAT

**ፍርድ ቤቱ የራሱን ውሳኔዎች በማስፈጸም ረገድ ያለው ስልጣን**

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ከካፒታል ገበያ ስርዓቱ ጋር በሚያያዙ ጉዳዮች በሙሉ ባለስልጣኑና የባለስልጣኑን ተግባርና ስልጣን የሚያስፈጽም ሰው በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ላይ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሆኖ ያገለግላል። በመሆኑም ፍርድ ቤቱ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች በሙሉ የተከራካሪዎችን የመሰማት መብት ያከበሩና ያረጋገጡ፣ አግባብነት ባላቸው ህጎችና ማስረጃዎች ላይ የተመሰረቱ ሊሆኑ ይገባል። እንዲሁም ፍርድ ቤቱ ተገቢ ውሳኔ ለመስጠት በሚያስፈልገው ልክ የሌሎች ተቋማትን እገዛ እና ድጋፍ ሊያገኝ ይገባዋል።

በዚሁ አግባብ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን፣ ብይኑን ትእዛዙን እንዲሁም የችሎት አካሄዱን ለማስፈጸም ይቻለው ዘንድ በፍትብሄር ስነ ስርአት ህጉ ለመደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ስልጣን ተሰጥቶታል። በመሆኑም መጥሪያ የማውጣት እና በመጥሪያው መሰረት ማንኛውም ሰው እንዲቀርብ የማስገደድ እንዲሁም በቃለ-መሃላ ምስክርነቱን (የሞያ ምስክርነትን ጨምሮ) እንዲሰጥ የማድረግ እና የመመርመር፤ ለሚሰጠው ፍርድ ወይም ብይን ወይም ትእዛዝ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች እንዲፈለጉ እና እንዲቀርቡለት የማዘዝ፤ የሚሰጠውን ውሳኔ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ትእዛዞችን እና እግዶችን የመስጠት እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን የመፈጸም ስልጣን ተሰጥቶታል።

አስተዳደር ፍርድ ቤቱ አንድ መደበኛ ፍ/ቤት በሀገሪቷ በፍትሐብሔር ጉዳይ በሕግ የተሠጠዉ ስልጣን በአዋጅ ተሰጥቶታል። አስተዳደር ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኝ ማቅረብ የሚችለው ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆኑ አስተዳደር ፍ/ቤቱ የፌደራል መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን እንዳለው ያሳያል። የፍ/ቤቱ አባላት የቀረበላቸውን ጉዳይ ከመመርመር አንጻር እንደአስፈላጊነቱ የመደበኛ ፍ/ቤት አካሄድ የሚጠቀሙ ሲሆን በመደበኛ ፍ/ቤት ዳኞች ያላቸው ስልጣን ይኖራቸዋል። ስለሆነም ትዕዛዝ ለማስፈጽም ፖሊስ የማዘዝ፣ የባለሙያ ምስክር መስማት እና ማንኛዉንም ምስክር አስቀርቦ የመስማት ስልጣን አላቸው።